# የድርጊት መርሐ ግብር (ፖሊሲ)

# የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ

**ተዛማጅ ምንጮች፦** ABC, ABC-RA, IEA, IEB, IED, IEF, IEF-RA, IKA-RA, IKB-RA, IKC-RA, JEA-RA
**ኃላፊነት ያለው ጽ/ቤት፦** ሥርዓተ ትምህርት ማስተማር እና ፕሮግራሞች
የአካዳሚ ዋና ኦፊሰር

## የውጤት አሰጣጥና ሪፖርት

### A. ዓላማ

የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ ለሁሉም ተማሪዎች ጠንካራ የአፈጻጸም እና የስኬት ደረጃዎችን ለመጠበቅ እና ለተማሪዎች እና ለወላጆቻቸው/ለአሳዳጊዎቻቸው ግንዛቤ እና ለትምህርት ዓላማዎች ተገቢ የሆነ የተማሪን እድገት ለመገምገም እና ሪፖርት ለማድረግ ፍትሃዊ ሂደት ለማከናወን ቁርጠኛ ነው።

### B. ጉዳዩ

የማርክ ውጤቶች የተማሪን ትምህርታዊ እርምጃ ለማስገንዘብ አስፈላጊ መንገዶች ናቸው። ስለዚህ የውጤት አሰጣጥ እና የሪፖርት አሠራሮች የሚከተሉትን ማካተት አለባቸው፦

1. ለተማሪዎች የትምህርት ዓላማዎች ለወላጆች/አሳዳጊዎች፣ ለአስተማሪዎች፣ ለአስተዳዳሪዎች እና ለትምህርት ሥርዓቱ በተማሪ ስኬት ላይ ትርጉም ያለው ግብረመልስ ተገቢ መረጃ መስጠት አለበት
2. ከሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሥርዓተ ትምህርት ጋር ማጣጣም
3. በት/ቤቶች ውስጥ እና በመካከላቸው ያለውን የአፈጻጸም ልዩነቶች ለማጥበብ እና ወጥነት ባለው ሁኔታ ተጠያቂነትን ለማስፈን
4. በግምገማዎች እና በአስተማሪ የተቀየሱ ተግባራት ላይ እንደሚታየው በትምህርት ሥርዓቱ ውስጥ ከተዘረዘሩት የክፍል ደረጃ አፈጻጸም ወይም የሚጠበቅ የኮርስ ውጤት ጋር ሲነጻጸር የተማሪን ውጤት ትክክለኛ ነፀብራቅ ማሳየት
5. በአስተማሪ የተዘጋጁትንና እንዲሁም በማዕከል የተዘጋጁትን ጨምሮ በተለያዩ ምዘናዎች ከጊዜ ወደ ጊዜ የተማሪው(ዋ)ን አፈፃፀም ትክክለኛ ፍትሃዊ ውክልና እንዲኖር ማድረግ
6. ለወላጆች/አሳዳጊዎች እና ለተማሪዎች ስለ ውጤት አሰጣጥ መመዘኛዎች እና ተዛማጅ ጉዳዮች ግልፅ እና ወቅታዊ ግንኙነት ማድረግ
7. ጥራት ያለው የመማር ተሞክሮ አስፈላጊ አካል እንደመሆኑ በትምህርት ቤት የመገኘት ቁርጠኝነት
8. የማርክ መስጫ ጊዜ ምዘናዎች፣ የዩኒት መጨረሻ ፈተናዎች፣ የማጠቃለያ ምዘናዎች፣ ፕሮጀክቶች፣ በአፈጻጸም ላይ የተመረኮዙ ምዘናዎች፣ እና ሌሎች ተመሳሳይ የተማሪ የክፍል ደረጃን የማሟላት ብቃት እና አጠቃላይ ማሳያዎችን የሚያካትቱ ግምገማዎችና የኮርስ ቁሳቁሶች
9. ለተማሪዎች በስርዓተ ትምህርቱ ውስጥ የተዘረዘሩትን የክፍል ደረጃ ወይም የሚጠበቅ የኮርስ ውጤቶችን

ችሎታ በተለያዩ ዘዴዎች የማሳየት ዕድል መስጠት

10. ስለ ተማሪው(ዋ) ወደፊት መጓዝ እርምጃ ለሁሉም ተማሪዎች እና ወላጆች/አሳዳጊዎች መደበኛ እና ተደጋጋሚ መረጃ መስጠት

11. ከሁሉም ተማሪዎች በሁሉም ኮርሶች እና ፕሮግራሞች ሁሌም ከፍተኛ ውጤት መጠበቅ

C. ሁኔታ

1. በሁሉም ትምህርት ቤቶች

a) መምህራን እነዚህን ግቦች ለማሣካት የተማሪ የተሟላ እውቀት እና ፈተናዎችን ጨምሮ ልዩ ልዩ ተግባሮችን ለማሳካት የ MCPS የሥርዓተ ትምህርት ማዕቀፍ እና የማስተማር መመሪያዎችን ይጠቀማሉ።

b) ተማሪዎች እና ወላጆች/አሳዳጊዎች በኮርስ መጀመሪያ ወይም በማርክ መስጫ ክፍለ ጊዜ በእያንዳንዱ ኮርስ ወይም ዩኒት ሥርዓተ ትምህርት የተዘረዘሩትን የሚጠበቅበቅባቸውን እና የተማሪዎች አፈፃፀም ስለሚገመገምበት መሥፈርት ይነገራቸዋል።

c) ተማሪዎች እና ወላጆች/አሳዳጊዎች በማርክ አሰጣጥ ወቅት በሙሉ አንድ ተማሪ ስለሚያሳየው የትምህርት አፈጻጸም እርምጃ መምህራን እንደዚህ ዓይነቱን መረጃ በየጊዜው በመደበኛነት እንዲያሳውቁ በጥብቅ ይበረታታሉ። የታየው እድገት ቢያንስ በየዘጠኝ ሳምንቱ በመደበኛነት ሪፖርት ይደረጋል።

d) መምህራን መደበኛ ባልሆነ እና በመደበኛ ሁኔታ ሪፖርት የተደረጉ ስኬቶችን የሚያረጋግጡ ቀጥተኛ እና ትክክለኛ ሪኮርዶችን ይይዛሉ።

e) የተማሪ እድገት በስርዓተ ትምህርቱ ውስጥ በተዘረዘሩት ወይም በልዩ አማራጭ ሥርዓተ ትምህርት ውስጥ ከተቀመጠው የክፍል ደረጃ እና የሚጠበቁ የኮርስ ውጤቶች ጋር የሚዛመዱ በርካታ እና የተለያዩ የግምገማ መለኪያዎች ከአፈፃፀማቸው አንፃር እየተገመገመ ሪፖርት ይደረጋል።

2. የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች

መደበኛ ሪፖርት በስርዓተ ትምህርቱ ላይ ከተቀመጠው የክፍል ደረጃ ከሚጠበቀው ውጤት ጋር በንጽጽር የተማሪን ውጤት በትክክል ያንፀባርቃል።

3. የመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች

መደበኛ ሪፖርት፣ በደብዳቤው እንደተገለጸው በስርዓተ ትምህርቱ በተቀመጠው መስፈርት መሠረት በትምህርቱ(ቷ) አፈጻጸም የሚጠበቁትን የተማሪው(ዋ)ን ውጤት ሪፖርት ያደርጋል።

4. የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች

a) መደበኛ ሪፖርት አሠጣጥ፤ በደብዳቤው ላይ እንደተገለጸው፣ በስርዓተ ትምህርቱ የተዘረዘረውን መሥፈርት መሠረት በማድረግ ከተማሪ የሚጠበቀውን የኮርስ አፈጻጸም ውጤት ሪፖርት ያደርጋል።

b) ተማሪዎች በክፍል ደረጃቸው የተካተቱና የሚጠበቅባቸውን የተቀናጀ የኮርስ መስጫ ቁሳቁሶች

ግንዛቤ ደረጃ/ችሎታ የማሳየት እድል ይሰጣቸዋል።

c) በመማር ማስተማር ሂደት አዘውትሮ መገኘት መከታተል እና ንቁ ተሳትፎ ማድረግ በክፍል ውስጥ ችሎታና እውቀትን የማጋራት ክንውን የትምህርታዊ ጥራት ተሞክሮ አስፈላጊ አካል እንዲሆን ያደርጋል። የኮርስ ቁሳቁሶችን የመገንዘብ ችሎታን ለማዳበር/ለማሳየት እና ስለትምህርቱ ክሬዲት ለመቀበል አዘውትሮ መገኘት እና ተሳትፎ ማድረግ ያስፈልጋል።

**D. *ተፈላጊ ውጤቶች***

የውጤት አሰጣጥ እና ሪፖርት የማድረግ ተግባሮች ፍትሃዊ እና ትርጉም ያለው እና ለሁሉም ተማሪዎች ጠንካራ የአፈፃፀም እና የስኬት ደረጃዎችን የሚደግፉ መሆን አለባቸው። ውጤቶች በትምህርት ሥርዓት ውስጥ ወጥነት ያለው ትርጉም ይኖራቸዋል እንዲሁም በስርዓተ ትምህርቱ በተቀመጠው መስፈርት መሠረት በክፍል ደረጃ እና በኮርስ እንዲሟሉ የሚጠበቁ ናቸው።

**E. *ግምገማና ሪፖርት***

ይህ ደንብ በቦርድ የማሻሻያ መመርያ መሰረት ክለሳ ይደረግበታል።

***የዚህ ፖሊሲ ታሪክ፡-*** የፀደቀበት ውሳኔ ቁ. 258-72፣ ማርች 27 ቀን 1972 ዓ.ም. የውሳኔ ቁጥር. 365-73፣ ጁን 12 ቀን 1973 ዓ.ም. የውሳኔ ቁጥር. 514-75፣ ጁላይ 15 ቀን 1975 ዓ.ም. የውሳኔ ቁጥር 397-77፣ ጁን 14 ቀን 1977 ዓ.ም. በውሳኔ ተሻሽሏል። 484-79፣ 485-79፣ 487-79፣ እና 492-79፣ ሜይ 10 ቀን 1979 ዓ.ም. በውሳኔ ተሻሽሏል። 613-81፣ 615-81፣ እና 616-81፣ ኦገስት 24 ቀን 1981 ዓ.ም. በውሳኔ በሌላ ይዘት ተተክቷል 333-86, ጁን 12 ቀን 1986 እና በውሳኔ ቁጥር 458-86፣ ኦገስት 12 ቀን 1986 በውሳኔ በሥራ ላይ እንዲውል ተደርጓል። 518-86፣ ሴፕቴምበር 22 ቀን 1986 ዓ.ም. በውሳኔ ቁጥር. 318-93፣ ኤፕሪል 14 ቀን 1993 ዓ.ም. በውሳኔ ቁጥር. 153-03፣ማርች 24 ቀን 2003 ዓ.ም. በውሳኔ ቁጥር 493-15፣ኖቬምበር 10 ቀን 2015 ዓ.ም ማሻሻያ ተደርጎበታል።